## የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በጥርና የካቲት ወራት የወሰዳቸው እርምጃዎች አጠቃላይ ሪፖርት

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል ባለፉት የጥርና የካቲት ወራት በጠላት ሃይል ላይ በወሰዳቸው የተለያዩ አይነት እርምጃዎች በእስሮች የሚቆጠሩትን የወያኔ ጦር አባላትን ሙትና ቁስለኛ አድርጎ ወታደራዊ ንብረቶቹንም በመደምሰስ ድል አስመዝግቧል። ከተገደሉት መካከል ቢያንስ አምስቱ ህዝብን በማዋከብ የሚታወቁ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የጠላት ካድሬዎችና ሰላዮች ናቸው። ወታደራዊ እርምጃዎቹ የትና መቼ እንደተወሰዱ እንደሚከተለው ተዘርዝሯል።

*ጥር 28, 2013- ፊንፍኔ ዙሪያ ገላን ጉዶ ቀበሌ*

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በተጠቀሰው እለት ከጠዋቱ 2፡15 ላይ በፊንፍኔ ዙሪያ ገላን ጉዶ ቀበሌ ውስጥ የየካ ክፍለ ከተማ ጽዳትና ውበት ቢሮ ምክትል ሃላፊ በሆነው ሽፈራው ገረመው በተባለው የወያኔ ቀንደኛ ካድሬ ላይ የመጨረሻ እርምጃ ወስዷል። ይህ የመንግስት ካድሬ በሚሰጠው ትእዛዝ ከፊንፍኔ ከተማ የሚወጣው የሽንት ቤት ፍሳሽ ቆሻሻ በገላን ጉዶ ቀበሌ ነዋሪዎች ቀዬ ላይ ሲጠራቀም በመቆየቱ ነዋሪዎች ይህ ህገ ወጥና የጤና ጠንቅ የሆነ ተግባር እንዲቆምላቸው በተደጋጋሚ ቢያመለክቱም ሰሚ ጆሮ ኣላገኙም። ካድሬው ለህዝቡ ጥያቄ በንቀት የተሞላ ምላሽ ከመስጠቱም በተጨማሪ ጥያቄውን ለማፈንና ጠያቂዎቹን ለማስፈራራት ወደ ቀበሌው እየተንቀሳቀሰ ሳለ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል የቅጣት እርምጃ ተወስዶበታል። እርምጃው በተወሰደበት ወቅት የካድሬው ሾፌርም መቁሰሉ ታውቆአል።

*ጥር 25, 2013- ምእራብ ሓረርጌ ሚኤሶ ወረዳ*

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በዚህ እለት በሚኤሶ ወረዳ ኦዳ ሮባ ቀበሌ የ50 ኣለቃነት ማእረግ ባለው የወያኔ ፖሊስ መኮንንና ቀንደኛ ሰላይ በሆነው ግብረ አበሩ ላይ የማያዳግም እርምጃ ወስዷል። በዚህ እርምጃ የተገደለው የፖሊስ መኮንን ብርሃኑ በመባል የሚታወቅ (የኣባቱ ስም ለጊዜው ያልታወቀ) ሲሆን ግብረ አበሩ የሆነው ቀንደኛው ሰላይ ደግሞ ሃሰን ሁሴን የተባለ መሆኑ ተመዝግቧል። የፖሊስ መኮንኑና ቀንደኛው ሰላይ የኣካባቢውን ነዋሪዎች ለረጂም ጊዜ በማስፈራራትና በማዋከብ የሚታወቁ ናቸው።

*ጥር 26, 2013- ድሬዳዋ ከተማ*

በድሬዳዋ ከተማ በተለምዶ ሳቢያን እየተባለ በሚጠራው ሰፈር የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በተጠቀሰው እለት በወሰደው ወታደራዊ እርምጃ፣

1. ሲሳይ (የኣባቱ ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
2. ኣብነት ሃጎስ እና
3. ታደሰ ጌትነት

በተባሉ የወያኔ ደህንነት ሹማምንት ላይ ጥቃት አድርሷል። በጥቃቱም ሲሳይ የተባለው የደህንነት ሹም ወዲያው ሲገደል የተቀሩት ሁለቱ በፅኑ ቆስለዋል። ሶስቱም የደህንነት ሰዎች በሳቢያን ኣካባቢ ነዋሪዎች ላይ ያልተቋዋረጠ የማስፈራራትና የማዋከብ ተግባር በመፈጸም የሚታወቁ መሆናቸውን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል አስገንዝቧል።

*የካቲት2, 2013- ምስራቅ ወለጋ- ሃሮ ሊሙ ወረዳ*

በዚህ ዞን ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በተጠቀሰው እለት ሃሮ ሊሙ ወረዳ ልዩ ስሙ ኣባ ሞኣ በተባለ ስፍራ በእንቬስተርነት ስም የኣካባቢውን ህዝብ መሬት በሃይል ነጥቀው በሰፈሩ፣

1. ለዊ በየነ (ባለ ሃብት)
2. ኣድማሱ ባርናባስ (ባለ ሃብት) እና
3. ጫኔ ኣሰፋ (የባለሃብቶቹ ደህንነት ጠባቂ)

በተባሉት የወያኔ ዘራፊዎች ላይ በወሰደው የእርምት እርምጃ በጽኑ ኣቁስሎኣቸዋል። እርምጃው በተወሰደበት ወቅት ሰሌዳ ቁጥሩ *ኢ.ኢ.04374* የሆነ የእርሻ ትራክተርም ጋይቷል። እንቬስተር ተብዬዎቹ የግል ሃብት ለማካበት ሲሉ የኣካባቢውን ነዋሪ ህዝብ ከመዝረፍና ከማስፈራራት በተጨማሪ ለወያኔ መንግስት በሰላይነት የሚያገለግሉ መሆናቸውም ታውቋኣል። በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል የተወሰደው ይህ እርምጃ ነዋሪውን ህዝብ ያስደሰተ ሲሆን በጠላት ላይ ደግሞ ድንገተኛ ድንጋጤ መፍጠሩ ተረጋግጧል።

*የካቲት 5, 2013- ምስራቅ ወለጋ- ሳሲጋ ወረዳ*

በተጠቀሰው እለት በኣካባቢው የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል ሳሲጋ ወረዳ ውስጥ የወያኔ ቀንደኛ ሰላይና ካድሬ በመሆን ለረጂም ጊዜ ነዋሪውን ህዝብ በማስፈራራትና በማዋከብ በሚታወቀው ተወልደ ኤሊያስ በተባለ ግለሰብ ላይ የማይዳግም እርምጃ ወስዷል። እርምጃው የተወሰደው ከነቀምቴ ከተማ 26 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ በምትገኘውና ልዩ ስሟ ጎቶ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ መሆኑ ተጠቅሷል። የስለላ ስራም ደርቦ በማካሄድ የሚታወቀው ይህ የጠላት ካድሬ ጊዳ፣ ጉቶ ዋዩ፣ ዲጋ ሳሲጋ እና ሄባንቱ ወረዳዎች ውስጥ በመዘዋወር በርካታ ሰላማዊ ነዋሪዎችን በሃሰት ወንጅሎ በማሳሰርና በማሰቃየት የሚታወቅ ነው። እርምጃው የተወሰደበት እለት ግለሰቡ በኣንድ ነጋዴ የጭነት መኪና ተሳፍሮ ወደ ሳሲጋ ወረዳ እያመራ እንደነበረ ታውቋኣል። እርምጃውን የወሰደው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ቡድን ወንጀለኛውን ያሳፈረውን ሾፌር ሳይጎዳ ኣስፈላጊ የንቃተ ህሊና ትምህርትና ምክር በመስጠት ሸኝቶታል።

*የካቲት 18, 2013- ምእራብ ሃረርጌ- ሚኤሶ ከተማ*

በምስራቅ ኦሮምያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በተጠቀሰው እለት ሚኤሶ ከተማ ውስጥ ንብረትነቱ የኣንድ ወያኔ ሰላይ በሆነ ሼል የነዳጅ ማደያ ላይ ጥቃት ኣድርሷል። የነዳጅ ማደያው ባለቤት ኣቦ በመባል የሚጠራ ሲሆን በባለ ሃብትነት ሽፋን እየተንቀሳቀሰ ለወያኔ መንግስት የስለላ ተግባር የሚያከናውንና በዚህም በርካታ ንጹሃን ዜጎችን በማሳሰርና በማስገደል የሚታወቅ ነው። ከዚህ እኩይ ድርጊቱ እንዲገታም በተደጋጋሚ ሲሰጠው የቆየውን ምክር ኣሻፈረኝ በማለቱ በንብረቱ ላይ እርምጃው ተወስዷል።

*የካቲት 18, 2013- በሚኤሶ ወረዳ ህዝባዊ እርምጃ*

ሚኤሶ ወረዳ ልዩ ስሙ ቦርደዴ እየተባለ በሚጠራ ስፍራ የወያኔ የጥፋት መልእክተኞች ሆነ ብለው በኦሮሞና ሶማሌ ነዋሪዎች መካከል ግጭት ከጫሩ በሁዋላ ሶማሌዎቹን የወገኑ በማስመሰል ትጥቅ ኣልባ የሆኑትን የኦሮሞ ነዋሪዎች በመምታትና በማስመታት ዘግናኝ ጉዳት ኣድርሰዋል። በዚህ ወቅት ህዝቡ ባደረገው የተባበረ ራስን የመከላከል እርምጃ ከወያኔ የጥፋት መልእክተኞች 7ቱን ሲገድል 9ኙን ማቁሰሉ ተረጋግጧል።

*የካቲት 19, 2013- ሚኤሶ ወረዳ*

በዚህ እለት በወታደራዊ ተሽከርካሪ ተጭኖ ግጭት ወደተነሳበትና ግጭቱን በጫሩ የስርኣቱ የጥፋት መልእክተኞች ላይ የተወሰደውን ህዝባዊ እርምጃ ለመበቀል ሲንቀሳቀስ በነበረ የወያኔ ጦር ላይ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል መንገድ ላይ በወሰደው የደፈጣ ጥቃት ጦሩን ከነተጫነበት ተሽከርካሪ ጋር ደምስሷል። በተሽከርካሪው ላይ ተጭኖ የነበረው ጦር ቁጥር ለጊዜው ባይታወቅም እርምጃው ጠላትን በእጅጉ እንዳስደነገጠው ታውቆኣል።

*የካቲት 23, 2013- ምስራቅ ወሊጋ- ሃሮ ሊሙ ወረዳ*

ምእራብ ኦሮምያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በሃሮ ሊሙ ወረዳ ልዩ ስሙ ትክሻ በመባል በምታወቅ ስፍራ ለኣሰሳ በተሰማራ የወያኔ ጦር ላይ ባደረሰው የደፈጣ ጥቃት ኣራቱን ገድሎ ሶስቱን ኣቁስሏል። በእርምጃው ወቅት ሁለት ኤኬ47 ጠብመንጃዎችም ከጠላት እጅ ተማርከው የነጻነት ትግሉ ንብረት ተደርገዋል።

*ህዝባዊ እርምጃ*

በሌላ ዜና ደግሞ የሃሮ ሊሙ ወረዳ ነዋሪ ህዝብ በወሰደው ህዝባዊ እርምጃ የወረዳውን ፍርድ ቤትና የቀበሌ ጽ/ ቤቶችን በእሳት ኣጋይቷል። ፍርድ ቤት ተብዬው ኢ ፍትሃዊ በሆነው ኣሰራሩ በርካታ ንጹሃን ዜጎችን በሃሰት እየወነጀለ በማሳሳር የሚታወቅ በመሆኑና የቀበሌዎቹ ኣስተዳደር ኣካላትም ከህግ በላይ በመሆን ያሹትን ኢ ፍትሃዊ እርምጃ በነዋሪዎች ላይ በመውሰድ የሚታወቁ በመሆናቸው ነዋሪው ህዝብ ለመንግስት ያለውን ኣንገዛም ባይነቱን ለማሳየት እርምጃውን እንደወሰደ ታውቆኣል።

ባጠቃላይ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ባለፉት ሁለት ወራት በተላያዩ የኦሮምያ ኣካባቢዎች በወሰዳቸው ወታደራዊ እርምጃዎች 5 ከፍተኛ የጠላት ካድሬዎችና ሰላዮችን ጨምሮ በኣስሮች የሚቆጠሩ የጠላት ሃይል ኣባላትን ሙትና ቁስለኛ ኣድርጎኣል። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተጠቀሱትን የጠላት ንብረቶችንም በማውደም ድል ኣስመዝግቧል። ፍትህን የተነጠቀውንና ሰላማዊ የትግል መንገድ የተዘጋበትን ህዝብ መብት ለማስከበር ሲባል የሚወሰደው ወታደራዊ እርምጃ በመላው ኦሮምያ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት እዝ ኣስገንዝቧል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!